# <u>በቃ በለን ይብቃን</u> !

የዘመናት ፍዳ ትውልድ ተቀባብሎ
ረሃብ ጠኔ ገኖ ሞት በሞት ተዛዝሎ
እንደ ዱር ጨንጊት ተጣብቆ ከሾክ ጋር
ዝማሪያችን ልቅሶ መጠሪያችን ችጋር ፤

አጥንት እየቆጠርን የዘር ሃረግ መዘን
በዘር ተከፋፍለን በመንደር ተውጠን
ጥማት እርዛቱ ረሃብ ሳያንሰን
እንደ አውሬ ተባላን ሰው መሆን ተሳነን ፤

ነገን የሚመኙ ሮጠው ያልጠገቡ
አገር ሰላም ብለው እንቧይ እየካቡ
እኩኩሉ እያሉ በደጅ ሲሯሯጡ
በሰው መሳይ አውሬ በድንገት ተዋጡ ፤

ጌታ በቃ በለን ይበቃል ብለናል
ደም ዘርተን ደም አጭደን ጎተራ ሞልተናል
አርባ ጉጉ፣ ወተር፣ በደኖ፣ ዶዶላ
ጊንቢ፣ ቄለም፣ቶሌ፣ ቡራዩ፣ ማይካድራ
በእሳት የነደዱት ያለቁት በካራ
ምነው ሰሚ ጠፋ ደማቸው ሲጣራ ፤

አይፈርድም አትበሉ ይፈርዳል ፈጣሪ
የዘራውን ያጭዳል ክፉና መሰሪ
ከምድር ወደ ሰማይ ይጮሀል ደማቸው
ዕሩቅም አይደለም ቅርብ ነው ፍርዳቸው ;

በሆድ ውስጥ ያለ ፅንስ በካራ ሲቀደድ
አካል ሲበጣጠስ ስጋ በእሳት ሲነድ
እናት ልጇን አዝላ ጥሻ ውስጥ ተደፍታ
ቀባሪ እንኳን ጠፍቶ ባሞራ ተበልታ
የጭካኔውን ጥግ ምን ብዬ ልናገር
ትላንት አላየሁም ወደፊትም አይኖር፤

ንገሪኝ ወለጋ ወገን ምን አጠፋ፤ ልጆች ምን በደሉ
በምን ጥፋታቸው በካራ ተቀሉ
ጭራቅ ተወልዶብሽ የሰው አረመኔ
ዋይ እንዳለ ቀረ አለቀ መገኔ

ዕሙ ትንሽቷ
ነገን ልታይ ጓግታ
በብሩህ ፈገግታ
ሕልሟ ተቀጨባት መንገዷ ተዘጋ ፤

መርጣ አልተፈጠረች ልሁን ብላ አማራ
የዘር ሃረግ መዛ ደምና አጥንት ቆጥራ
ወላሂ ከእንግዲህ አማራ አልሆንም ብላ ስትማፀን
በዱኗ እየማለች እንዲያ ስትለምን
አላሕን ብትጠራም በኮልታፋ አንደበት
አማራ መሆኗ ዳረጋት ለሕልፈት ፤

ቄለም ያስገዘፈሽ ዛርሽ አላገኝም ምሱን
አጋግመሽ ከርቤ ዕጣን ጭሳጭሱን
አልረጋጋ ቢል አውሊያሽ አምርሮ
የሰው ሥጋ ዕጣን ሆነልሽ ዘንድሮ ፤
ልጆችሽን ያጣሽ አንቺ ወላድ እናት
በእሳት የነደድከው አንተ ጀግናው አባት
ያለአባት ያለእናት የቀራችሁ ልጆች
እግዚአብሔር ያፅናችሁ
ፊቱን ያብራላችሁ፤
ወላሂ አማራ አልሆንም፤ አልሽ ቢጨንቅሽ
ኮለል እያለ እንባሽ በጉንጮችሽ
እየተርበተበተ ከንፈርሽ
እየራደ ሰውነትሽ ፤
ከሞት ጋር ተፋጠሽ ከአራዊት መንጋ
ጠብሶ ከሚበላ የሰው ሥጋ
አይታሰብ ምህረት
ከሰው መሳይ አውሬ ፍጥረት፤
በአኖሌ ተረት
በጨለንቆ ትርክት
በበድን ሃውልት
መልዕክት አልባ ጥፍጥፍ ድንጋይ
በቀል ሊያጭር አገር ሊያጋይ፤
ድንጋይ ድንጋይን ሰርቶ
አኖሌ ላይ ጎልቶ
ትውልድ አባላ አናክሶ
ደም አቃባ አጫርሶ ፤
አልሸተተሽም ወለጋ
የሰው ሥጋ
የሕፃናት ያለግላጋ
እንደ በከል የጠበሸው
የሰው አጥንት ያከሰልሽው ፤
ደም ጠጥተሽ
ሞራ አቃጥለሽ
አውልያሽን አረጋግተሽ
አሁን ረካሽ ፤
እያስጓራ የደም ጥማትሽ
የሰው ሥጋ ምስሽ
ቃል ለምድር ለሰማይ ከእንግዲህ ይበቃል
ጀግኖች በሞሉበት ቤት፤ አማራ እንዴት ያልቃል ?
ጌታ በቃ በለን ይበቃል ብለናል
ደም ዘርተን ደም አቾደን ጎተራ ሞልተናል
አሣር በረከተ መከራችን በዛ
ይብቃ በለን በቃ አለቅን እንደዋዛ ፤

የሰይጣንን ሥራ ቀድሞ ስላወቁ
ሼኩም ወደመስጊድ ሄደው ቢደበቁ
ነብሰ በላው አውሬ አረመኔው ቡድን
አንድም ሰው ሳያስቀር ፈጀው ቤተሰቡን ፤
አላህ ለምን ተውከኝ
ምነው ብትወስድኝ
አዝነው አለቀሱ ከአንጀት ምርር ብለው
አስራሁለቱንም በአንድ ጉድጓ ቀብረው፤
ሕፃናቱን በሰልፍ በአንድ ላይ ኮልኩለው
ዳቦ እንደሚያካፋፍል አዛኝ ሩህሩህ መስለው
ጨፍጭፈው ጣሏቸው በጥይ እሩምታ
የሚስኪኖች አምላክ ውረድ ፍረድ ጌታ ፤
አባቶች አነቡ ሕፃናት አለቁ
ብዙዎች አለፉ ወላጆች ወደቁ
ማን ለማን ይከሰስ ማነው ፍርድ ሰጭ
አባቱ አንኳሪ ልጅዬው በጥባጭ፤
አጥንት ተፈለጠ ሥጋ ተበለተ
ጨኸት አስተጋባ ዋይታ በረከተ
ምን ተሰማሽ ቄለም አንቺ የደም ጎራ
ሕፃናት ሲወጉ ሲቀሉ በካራ
ዕኮ ምን ተሰማሽ ?
አለሽ ይሆን ምላሽ ፤
ምንስ ወንጀል ሰሩ እኮ ምን አጠፉ
ዕጌረዳዎች ለምን ተቀጠፉ
የጅብ መንጋ ወልደሽ ተኩላውን አንግሰሽ
ሕፃናት አስጨርሰሽ እናቶች አስፈጅተሽ
ንገሪኝ ወለጋ ተናገሪ ቄለም
የሞተው ሰው እንጂ የአወሬ ልጅ አይደለም
ደምን በደም ቢያጥቡት ተመልሶ ደም ነው
ሆኖ እንጂ ብሒሉ
ለኛም ቀላል ነበር ብረት መወልደሉ፤
እንግዲህ ይበቃል
አንዱ እያለቀሰ አንዱ እንዴት ይሰቃል
ደም እየፈሰሰ
ቤት እየፈረሰ
አይሆንም በጭራሽ
ይሰጠዋል ምላሽ ፤
እናንት የቀን ጅቦች
ጨፍጫፊ ቡልጉዎች
የሕፃናቶቹ ይፍረድ ደማቸው
አፅም ሥጋቸው ፤
የአድዋው ባለሟል የጀግኖች ውሃ ልክ
የጥቁር ሕዝብ ፈርጥ እምዬ ሚኒልክ
ሲያወሩ ሲያስወሩ ተርት እንቶፈንቶ
ሲቀዱ ሲሰፉ የታሪክ ቡትቶ ፤

ገዳይ ማን እደሆን ጡት ቆራጭ ጭራቅ
ይሄው ጊዜ አሳየን ውሉን አይስትም ሃቅ
በጅምላ ጨፍጭፎ ሬሣ የሚያቃጥል
ትንሽ ነው ትልቅ ነው ሴት ነች ሕፅን ሳይል
ደም ቀድቶ የሚጠጣ ስጋ ቆርጦ በሌ
ቄለም ወለጋ እንጂ አይደለም አኖሌ
ነፃነት ገፎ ግፍ ሰቅሎ እንደሰደቅ
ነፃ አውጪ ብሎ መሞላቀቅ
የዱር አውሬ መንጋ የደመነብስ ብዜት
በበታችነት ሰንሰለት ታስሮ በእግርብረት፤
ሩጫ መገደብ ሕልም ማጨናገፍ
በጥላቻ መለከፍ
በሳንጃ ቀዶ ፅንስ ማውጣት
በቁም ማቃጠል እሳት መከተት
የግፍ ጥግ የአረመኔነት ጫፍ
ሰው ማንደድ እንደጧፍ ፤
እናት ዓለም ከልጆችሽ ጋር ተቃቅፈፋችሁ
በአንድ ጉድጓድ ተኝታችሁ
አላምን አልኩት ዓይኔን
በሕልሜ ነው ብውኔ ፤
እዚህም ሬሣ እዛም ሬሣ
በየጫከው በየማሣ
ልጇን አዝላ ወድቃ አየኋት
ቀን የጣላት ሚስኪን እናት ፤
አውሬ ሲሆን ሰው ሲቀየር
ምን ጉድ ነው የጉድ አገር
አውጣን ጌታ ከመአቱ
ተቀይሯል ሰው ፍጥረቱ ፤
ቤነሻንጉል ፥ አሶሳ በደም የታጠብሽ ሽርቆሌ
የተቀለብሽ ሕፃን ሽማግሌ
ብድሩን አታጪ ደምን ደም ያመጣል
ይዘገያል እንጂ ፈጣሪ ይቀጣል ፤
የእናት ሆድ ዥንጉርጉር
አንዱ ገራም አንዱ ነብር
እርግብ አለ ደግሞም ኮብራ
ሽለምጥማጥ የሰው ቁራ
ከሞት አምልጣችሁ የተረፋችሁ
ቤተሰብ ያጣችሁ
ያለእናት የቀራችሁ
የልጅ ሞት ያንሰፈሰፋችሁ
ምን እንበል ሌላ ፈጣሪ ያፅናችሁ ።

// **ዳዲሞስ** //